<u>የረቡዕ ጥር 3   8 1998 ዓም ( ጃንዋሪ 11   2006)</u>

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## ኢትዮጵያና የታሪክ እንቆቅልሹ

የታሪክ ምፀትና እንቆቅልሽ ሰለባዎች  ከሆኑት በጣም ጥቂት የዓለም ሀገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ ሀገራችን ግምባር ቀደም ነች ብንል ከእውነት የራቀ አባባል ነው ሊባል የሚችል አይመስለንም፡፡  ከተባለ ግን የሚያሳመነን ከተገኘ ይቅርታ ከመጠየቅ ወደኋላ አንልም፡፡ እኛ ግን ይህን አባባላችን፥ የተቻለንን ያህል በማስረጃ እያስደገፍን ለመግለጽ መሞከራችን አይቀርም፡፡  ይህን የምናወሳውም ደግሞ፥ ለሀገራችን፥ ለሕዝባችን ለታሪካችንና ለወደፊት ዕድላችን ካለን መቆርቆርና መቆጨት  እንጅ፥ የሞራል ሥልጣኑ የኛ  ብቻ ነው ከሚል ግብዝነት አይደለም፡፡  በዕርግጥ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተበድሏል፥ ተጠቅቷል፥  ተዋርዷል፡፡ ከዚህም የተነሳ፥ ቆጭት አለበት፤ ሰቆቃ አለበት፥ የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የሩቅ ዘመድ የለውም፡፡ የሚያምናቸው መሪዎቹ በየጊዜው    ይበድሉታል ያዋርዱታል፥ ይጨቁኑታል፥ ይዘርፉታልም፡፡ በመጨረሻም ከድተው፥ ለሌላ በላዔ-ሰብ አጋልጠውት ጥለውት ይሄዳሉ፡፡ በቀውጢ ቀን፥ በወሳኝ ጊዜ፥ ሰማይ ምድሩ በሚደፋበት ወቅት፥  ጉም አድረገውት ይሸሻሉ፡፡  መሪዎቹ፥ በሥልጣን በሚቆዩበት ዘመን፥ <u>ተጠልቶ መፈራትን እንጅ፥ ተወድዶ መከበርን</u> <u>አይፈልጉም</u>፡፡  አምባገነኖች ሁሉ፥ ዘወትር በሕዝብ ዘንድ የተጠሉ መሆናቸውን ባይዘነጉትም፥  ዘለዓለም ተፍርተው የሚኖሩ ይመስለቸዋል፡፡ ሁል ጊዜ ሕዝቡ ፀጥ ለበጥ ብሎ የሚገዛላቸው ይምስላቸዋል፡፡ ኃይላቸው የሚሳሳ፥ ጉልበታቸው ሚደክም፥ ሥልጣናቸው የሚከስም፥ ቀናቸው የሚጨልም፥ ጊዜያቸው የሚያከትም ፈፅሞ አይመስላቸውም፡፡ በሕዝብ አመፅ በአፍ-ፀጢማቸው የሚደፉ መሆናቸውን ጭራሽ አይታያቸውም፡፡

የሕዝብ ኃይልና ሥልጣን፥ የሕብረተሰብ  የመጨረሻው ወሳኝ መሆኑ የሚያከራክር ባይሆንም፥ በኢትዮጵያ ሀገራችን ግን ይህ ሃቅ  እስከዛሬ ድረስ መከሰት ቀርቶ፥ ታልሞም አይታወቅም፡፡ ህልምን ወደዕውነት ለመለወጥ ግን ሕዝቡ  የሚሳነው ሆኖ አይቀርም፡፡፡ ይህን ማድረግ የሚቻለው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨምግጎ ከያዘው አባዜ ሲላቀቅ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህ አባዜ ደግሞ፥ የታሪክ ዕንቆቅልሽና የዘመናት ምፀት ነው፡፡  እነኝህን ቆራኛዎች ማስወገድ መቻል ይኖርበታል፡፡  ሁሉን ማድረግ የሚያስችለው ኃይልና ሥልጣን ሊኖረው ሲችል፥ ባምባገነኖች እየተገዛ ይኖራል፡፡ በልቶ ጠጥቶ መኖር የሚያስችለው ሁለንተናዊ የተፈጥሮ ሀብት ሞልቶ ተርፎት፥ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ በማጣት በምፅዋዕት  ዕድሜውን ይገፋል፡፡ በአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው የሰለጠነ የሰው ኃይል እያለው ያንን ሊጠቀምበት አልተቻለውም፡፡ በመላው ዓለም ተሰራጭቶ ሌላውን የሚያገለግል በተለያያ የሙያ መስክ የሰለጠነ  ምሁር እያለው፥ አልተገለገለበትም፡፡ ይህም ሌላው እንቆቅልሽ ሆኖበታል፡፡ ስንት ጀግና ስትፈጥር  የነበረችው ሀገር ዛሬ የወላድ መካን  ሆና የማንም መጫዎቻ

ሆናለች፡፡ በዘመነ-ቅኝ ግዛት፥ልዕልናዋ ያልተገሰሰ፥ ድንበሯ ያልተደፈረ ፥ ነፃነቷ ያልተተነኮለ፥ ባህሏ ያልተበረዘ፥ የጀግኖቿ ማንነት የተመሰከረ ሀገር፥ በአሁኑ ጊዜ እንዳልሆነች ሆናለች፡፡ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ በዴሞክራሲ ሥርዓት እየተስተዳደረ፥ ዛሬ በአምባገነን ከሚጨቆኑ ጥቂት ሀገራት አንደኛዋ ሆናለች፡፡ እንዲያው በደፈናው ሀገራችን ኢትዮጵያ የታሪክ ዕንቆቅልሽና የዘመናት ምፀት ሰላባ ነች ከማለት በስተቀር፥ እናም ደግሞ፥ ከነዚህ አባዜዎች ተላቅቃ እንዴት ጤናማ ሀገር ትሆናለች የሚለውን ብልሃት ከፈለግ በስተቀር፥ ምፀቶቿንና ዕንቆቅልሾቿን ዘርዝረን መጨረስ የሚቻለን አይመስለንም፡፡

በሌላ ረገድ ደግሞ፥ ምፀቶቹንና እንቆቅልሾቹን ምናልባት እኛው እራሳችን ፈጠርናቸው እንደሁ እንጅ፥ ከዚያም፥ አብረውን እንዲኖሩ ፈቀድንላቸው እንጅ፥ እነርሱ በራሳቸው የችግሮቻችን ምንጮች ናቸው ማለት አይደለም፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን/ያት የውስጥ ችግሯቻችን ለመፍታት ከመጣራችን አስቀድመን ፥ ችግሮቻችንንና ምንጮቻቸውን በሚጋባ መረዳት ይጠበቅብናል፡፡ የታማረው ክፍል፥ የፖለቲካ ድርጅቶችና የነቃሁ-የበቃሁ ነኝ የሚለው የኅብረተሰብ ክፍል ከራሱ ጋር እየታረቀ፥ ከሌላው ወገኑ ጋር ታርቆ የጋራ ሀገሩን ችግር በጋራ ለመቋቋም እስካልቻለ ድረስ፥ የሀገራችን መሠረታዊና ውስብስብ ችግሮች ሊወገዱ ቀርቶ ሊቀረፈቱ ይችላሉ ማለት፤ ቢያንስ እራስን ማታለል ይሆናል፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ ይህን መገንዘብ ማለት፥ ለችግሮቻችን መፍተሄ ፍለጋ የመጀመሪያው ዕርምጃ ይመስለናል፡፡ ይህን ሳናደርግ ቀርተን፥ እንዲያው በደፈናው፥ ሌላውን እየወቀስንና በሌላው እያመካኘን መኖር የለብንም፡፡ ያለፉትንና አሁን የላውን የአምባገነን ሥርዓቶች እየወቀስን፥ እየኮነን፥ እያወገዝ መቀጠሉ ጭራሽ መፍተሄ አያመጣልንም፡፡ አንድ ትውልድ የራሱን የወቀቱን ችግር እራሱ የመፍታት ኃላፊነት፥ ግዴታና የታሪክ ተልዕኮ መሆኑን መረዳት መቻል አለበት፡፡ ወደ ምዕራባውያን ቢማመፀኑ፥ ወደምሥራቅ ቢዞሩ፥ ወደዓለም አቀፍ ተቋማት ቢያንጋጥጡ፥ ወደግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ቢማፀኑ መፍትሄ አይገኝም፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ፥ በምፀት ኖረሽ በእንቆቅልሽ ተከፍነሽ ተቀበሪ የተባለች ይመስል፥ ዛሬም ከዚህ ክስተት ሊተላቀቅ አልቻለችም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ከአምባገነን ሥርዓት ለመላቅቅ የደም መስዋዕት እየከፈለ ባለበት በዚህ የሞትና የሽረት ትግል ውስጥ መሆኑ ቢታወቅም፥ ትግሉን የሚያቀነባብርለትና የሚመራው ድርጅት እንደሌለ፥ ይኸው ግሃድ እየሆነ መጥቷል፡፡ ከአለፈው ሰኔ ሠላሳ ቀን ጀምሮ፥ ማንም፥ሳይቀሰቅሰው፥ ሳይመራውና ሳያግዘው ከዘረኞች አምባገነንን አገዛዝ ለመላቀቅ የራሱን አማራጭ በመውሰድ እነመለስ ዜናዊን እያርበተበተ ይገኛል፡፡ የሰላማዊ ዜጎች ደም በአደባባይ በመጉረፍ ላይ ነው፡፡ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶችም ይሁኑ የዴሞክራሲ ሀገሮች የሚባሉትም ጩኸቱን ሊሰሙለት፥ አቤቱታውን ሊያዳምጡለት፥ ሰቆቃውን ሊያዩለት ፈቃደኞች ሆነው አልተገኙም፡፡ ብለን ነበር ከሚል ስሌት በመነሳት፥ ከኋላ ተጠያቂነት ለማመለጥ ሲሉ ግን የይስሙላ የተቃውሞና የውግዘት መግለጫ ሲያወጡ እንሰማለን፥እናያለን፡፡ የተቃወሚ ድርጅቶችም፥ ቢሆኑ እንኳንስ እርሱን ሊመሩት፥ የትግሉም ተካፋዮች ሊሆኑለት ቀርቶ፥ እርስ በዕርሳቸውም

ቢሆን ተስማምተው የጋራ መግለጫ አማውጣት አልቻሉም:: አንዱ ያወጣውን መግለጫ ሌላው ሲያፈርሰው ይታያል:: አንዱ የወሳደውን አቋም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሌላው ሲቃረነው ይደመጣል:: በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የተከሰተው እንቆቅልሽና ምፀት፥ ከልክ ያለፈ መሆኑን የምነገነዘበው፥ ጋፍኛ፥ ሕዝቡ መሪ፥ የተቃዋሚው ክፍል ተመሪ መሆኑ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከራ ገመዱን በገዛ እጁ በጥሶ፥ የጭቆና ቀንበሩን ሰብሮ፥ ነፃነቱን ለማግኘት በሚያደረግው የሰላማዊ አመፅ ምክንያት፥ የወያኔ ነፍሰ-ገዳይ ሠራዊት በአደባባይ እየጨፈጨፈው ይገኛል:: ይህንን የሕዝብ ጭፈጨፋ በዘላቂ መልኩ ለማቆም የሚቻለው፥ ከሕዝቡ ጎን ቆሞ የሕዝቡን የመከላከል ኃይል ሲያጎለብቱና ሲያጠነክሩ ብቻ ነው:: ይህ ደግሞ በአሁኑ ወቅት ሲደረግ አይታይም:: እንዲያውም ተጨፍጫፊውን ሕዝብ እንደ አጥፊ፥ መለስ ዜናዊንና ነፍሰ ገዳዮቹን እንደ አልሚ እየተቆጠሩ ነው:: ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መከሰትና መስፈን ሲታገሉ የተጨፈጨፉትን ሰላማዊ ዜጎች፥ የበንክ ዘራፊዎች ናቸው ብሎ የተወሰደባቸው ርምጃ ትክክል ነው ብሎ መለስ ዜናዊ ሲናገር፥ ይህንን ሁኔታ አለማውገዝ ከመሰማዕታት ጎን አለመቆም፥ በህሊና በኩል የሚያስከትለውን ወቀሳ ለጊዜውም ቢሆን እንተወውና በታሪክና በትውለድ ዘንድ የሚያስፈርድና የሚያሰጠይቅ መሆኑን ግን ሳናስመዘግብ ማለፍ አንፈልግም::

ሰላማዊ የሆነውን ሕዝባዊ አመፅ አለመደገፍ ብሎም በመውገርግር ላይ ያለውን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ አውሽልሽሎ ለማቆየት የሚደረገው ጥረት የኋላ የኋላ በኃላፊነት የሚያስጠይቅ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል:: በዚህ የመከራ ዘመን በሚከፍለው የደም ዋጋ፥ ነገ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓተትን እንደሚመሠረት ማንም ሊጠራጠር አይገባም:: ይህን ክስተት ለማምጣት በሚደረግ የትግል ሂደት ሊወሰድ የሚቸለው ምርጫ ሁለት ብቻ እንደሆነ ለማመን እንፈልጋለን:: አንደኛውና ትክክለኛው፥ ከሕዝብ ጎን በመቆም አጋርነትን በተግባር ማሳየት ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ የሕዝቡ ሰላማዊ አመፅ ተኮላሽቶ እንዲቀርና የወያኔ የዘረኛ አገዛዝ እንዲቀጥል በሚደረገው ሂደት የወጀንሉ አባሪና ተባባሪ መሆን ነው:: ከየትኛው ጎን የመቆሙ ጉዳይ የእያንዳንዱ ውሳኔ ነው:: ፈቅዱ በሚወስደው ውሳኔም ተጠያቂው ያው እራሱ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን፥ አሁን የጀመረውን ትግል ሊያቆመው የሚችል ኃይል አለ ብለን አናምንም:: ዕርግጥ ይህ የአሁን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጊዜያዊ ፀገም፥ ወቅታዊ ድክመት ሊያጋጥመው ይችል ይሆናል:: ተዳፍኖ ግን ሊቀር የሚችል አይሆንም:: ይህንን መካድ ወይም አለመገንዘብ ማለት የታሪክን ሀቅ አለመረዳት ይሆናል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የሚፈለገው የማያወላውሉ፥ በዓላማቸው ፀንተው ቆራጥ ሕዝባዊ ውሳኔና አመራር የሚስጡ መሪዎችን እንጅ፥ የመለስ ዜናዊ ጨፍጨዘፊ ቡድን የጨፈጨፋቸው የመስዋዕታት ደም ሳይደርቅ አሳፋሪ ስምምነት የሚፈራረሙትን አይደለም:: መለስ ዜናዊ ቀኑ እንደቀረበ ማንም ሳይነግረው እርሱ እራሱ የተረዳው ሆኗል:: ሥልጣኑን ግን በሠላማዊ ሁኔታ ለሕዝብ ለማስረከም ፈቃደኛ አልሆነም:: አይሆንምም:: ያ እስከሆነ ድረስ ደግሞ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊኖረው የሚችለው ምርጫ የያዘውን ሰላማዊ አመፅ እያሰፈ፥ እያስፋፋ፥ እያጠነከረና እያቀነባበረ

መቀጠል ይሆናል፡፡ ለዚህም ሦስት ወሳኝ ጉዳዮችንበተግበር ልንተረጉም ይገባል፡-

1) የታሰሩት የፖሊቲካ መሪዎችና ሌሎች የኅሊና እስረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ በአንድ ልብ በአንድ ልሳን መናገር አለብን፡፡
2) ሁሉም የፖሊቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች፥ የሲቪክ ማኅበራትና ሊሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችያለምንም ምክንያትና ሰበብ በአንድ ላይ ቆመው ለብሄራዊ ነፃነትና ለሀገራዊ አንድነት በኅብረት መታከል አማራጭ የሌለው መሆኑን መማወቅ አለባቸው
3) የመለስ ዜናዊ የጎሳ ፖሊቲካ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተተፋ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ሀገሩን በጋራ አድኖ በጋራ አብሮ ለመኖር የሚያስችለውን ሥርዓት ለማምጣት፥ በጋራ አብሮ ተባብሮ መታገል፥ በአሁኑ ወቅት ወሳኝ ሆኗል፡፡

እኛም በበኩላችን፥ ይህን ሕዝባዊ አመፅ ለመደገፍና ከጎኑ ለመቆም ተልዕኳችን ስለሚያስገድድን የሕዝቡ ትግል እንዳይዳፈን የተቻለንን ሁሉ ከማድረግ የሚያግደን ምድራዊ ኃይል እንደሌለ ለሕዝባችን ቃላችን እንደገና እናሳድሳለን፡፡